ILRI
International Livestock Research Institute
www.ilri.org

Better lives through livestock

# የካውፒ (Cowpea) ተክልን ለከብት መኖነት በአነስተኛ እርሻ ላይ ማልማት

## ዓላማ:

በቆላማና መካከለኛ እርጥበት ባላቸው ቆላማ ቦታዎች ገበሬዎች ለሚያረቧቸው ከብቶች ጥራት ያለው የከብት መኖ ለማቅረብ ነው።

## የተክሉ ሁኔታ መግለጫ

- ጠንካራ ግንድ የሌለው ሀረግ መሰል ሆኖ ቅጠሎችና ፍሬዎች ያሉት በፍጥነት የሚያድግ በያመቱ የሚደርስ መኖ ነው፣
- የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች የሚስማሙት ሲሆን ድርቅን መቋቋም ይችላል፣
- የአፈር ለምነትን ለማሻሻል የሚበጅና ከሌሎች አገዳ እህሎች ጋር ሲዘራ ይችላል፣
- ከፍተኛ የገንቢነት ጥቅም ያለውና ለከብቶች በጣም ተስማሚ ነው፣
- እንደተቆረጠ እርጥቡ በሸክም ሲቀርብ ወይም ድርቆሽ መሆን ይችላል።

## ደካማ ጎኖች

- ከፍተኛ ግጦሽ መከልከል ይኖርበታል፣
- ቅዝቃዜ፣ ከባድ ዝናብ ወይም ውርጭ አይስማማውም፣
- በተባዮችና በበሽታ በቀላሉ የሚጠቃ ተክል ነው።

## አሠራር

የማሳ ዝግጅት

- በደንብ ታርሶ የተዘጋጀ መሬት ያስፈልጋል።

ዘር መዝራት

- በሄክታር 25–30 ኪ/ግ ዘር በአንድ ሄክታር መሬት ላይ በ3 ሴንቲ ሜትር ጥልቀት ዘርቶ ማልበስ ወይም ከ30 እስከ 60 ሳንቲ ሜትር በየመስመሩ መሃልና ከ10 እስከ 15 ሳንቲ ሜትር በየተክሉ መሃል እየተው መትከል ያስፈልጋል።



ማዳበሪያ

- በዘር ወቅት 100 ኪ/ግ ዳፕ ለአንድ ሄክታር መጠቀም፣

አጨዳ

- ሰብሉ አጎንብሶ ለአጨዳና ለማጓጓዝ እንዳያስቸግር  የአፎቱ ሁለት ሦስተኛው እጅ ደረቅ ሲልና ሲያነቃንቁት መንሿሿት ሲጀምር መቁረጥ ይቻላል። ከውቂያ በፊት ቅጠሉ በደንብ መድረቅ ይኖርበታል። ካውፒ ሲደረስ በእጅ ወይም በከብቶች ወይም በመሳሪያ ማጨድ ይቻላል።

ውጤት

- ከ12 እስከ 16 ሳምንታት ውስጥ ከ3 እስከ 10 ቶን ደረቅ መኖ በሄክታር ይሰጣል። ዘር ከተሰበሰበ በኋላ ተረፈ ምርቱ ለመኖነት

headquarters
PO Box 30709, Nairobi 00100, Kenya
Phone: 254 20 422 3000
Fax: +254 20 422 3001
e-mail: ilri-kenya@cgiar.org

principal site
PO Box: 5689, Addis Ababa, Ethiopia
Phone: +251 11 617 2000
Fax: +251 11 617 2001
e-mail: ilri-ethiopia@cgiar.org

Asia office
New Delhi 110 012, India
P +91-11 2560 9800
P +91-11 2560 9815 (direct)
F +91-11 2584 7884

ይውሳል። የተረፈ ምርቱ የፕሮቲን ይዘት ከ10–15% ሲሆን አበባ እንዳፈራ ከሆነ የፕሮቲን ይዘቱ እስከ 30% ሊደርስ ይችላል።

## ዘር ማባዛት

- የደረሱ የካውፒ ዘሮችን በየጊዜው በእጅ መልቀም ጥሩ ውጤት ያስገኛል። አማካይ ውጤት 750 ኪ/ግ በሄክታር ነው። ነገር ግን ጥሩ አያያዝ ከተደረገለት ማሳ በጥሩ አየር ጠባይ እስከ 1500 ኪ/ግ ዘር ሊገኝ ይችላል። ዘሩ በተባዮች እንዳይጠቃ ተስማሚ ፀረ ተባይ መጠቀምና በቀዝቃዛ ስፍራ ማኖር ያስፈልጋል።

## አጠቃቀም

- የካውፒ ተክልን በቡቃያው ወቅት በየ3 እና 4 ሳምንታት ጊዜ እየጠበቁ ርጥቡን በሸክም ለመኖነት ማቅረብ ይቻላል። በየ7 እና በየ8 ሳምንቱ ደግሞ ቆርጦ ድርቆሽ ማድረግና በሸክም ርጥቡን ከማቅረብ ጋር እያለዋወጡ መጠቀም ወይም ከ3 እስከ 4 ወራት ጠብቆ ቡቃያው ሲደርስ ቆርጦ ተረፈ ምርቱን ማግኘትም ሌላው አማራጭ ነው። ተክሉን ብቻውን ወይም ከሌሎች እንደበቆሎና ዘንጋዳ ካሉት ጋር አብሮ ማምረት ይቻላል። ካውፒ ለጥገቶች ከፍተኛ ጥራት ያለው መኖ ነው። ጥንቃቄ ከተደረገለት ጥሩ ድርቆሽ መሆን ይችላል። ግንዱ ቶሎ ስለማይደርቅ ጊዜ ወስዶ በጥንቃቄ ማድረቅ ተገቢ ነው። የካውፒ ተክል ከበቆሎና ከዘንጋዳ ጋር ሲደባለቅ ናይትሮጅን በማመንጨት ተረፈ ምርቱ በቀላሉ እንዲበላ ያደርጋል።

Information leaflet on livestock feeds and feeding technologies for small-scale farmers developed through collaboration between ILRI and its partners

June 2010

For further information, contact:
Fodder Adoption Project
fodderadoption.wordpress.com
Forage Diversity Project
International Livestock Research Institute,
PO Box 5689, Addis Ababa, Ethiopia
Email: a.duncan@cgiar.org or j.hanson@cgiar.org